# የአፋር ህዝብ ፓርቲ
# የጤና ስትራተጂ

APP - አህፓ ምርጫ 2013

# መቅድም

ጤና የአንድ ማህበረሰብ የእድገት ሞሶሶ ነው። ጤናማ ማህበረሰብ በትምህርትና በምርታማነት ዉጤታማ ከመሆኑም ባሻገር በተለያዩ ምክንያቶ የሚፈጠሩ ቀውሶችን ለመቋቋም ልዩ ችሎታ (resilience) እንዳለው የሕብረተሰብ ጤና ጥናቶች ያመላክታሉ። ለዚህም ነው ጤና የአንድ መስሪያ ቤት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ሴክተር መስሪያ ቤቶች የጋራ ሃላፊነትና በመስኩ የሚመዘገቡት አዎንታዊ ዉጤቶችም የጋራ ስራ ድምር ዉጤቶች ናቸው የሚባለው። የጤና ሴክተሩ መጠናከር የሚችለው የዉኃ ቢሮ የንጹህ ዉኃ አቅርቦትና ተደራሽነት ሃላፊነቱን በአግባቡ ሲወጣ፤ የተምህርት ቢሮ የትምህርት ተደራሽነትን የማስፋፋት ሃላፊነቱን በአግባቡ ሲወጣ፤ የግብርና ቢሮ በክልሉ ያለውን የምግብ እጥረት ለመቀነስና የተመጣጠነ የምግብ አቅርቦቶችን ሲያመቻች እንዲሁም የእንስሳት ጤና አጠባባቅ ግብአቶችን ሲያቀርብ፤ የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ የጤና ማዕከለኦችን በፍጥነት ለመድረስ የሚያስችል የመንገድ መረብ ሲዘርጋና የመልካም አስተዳደር ችግሮች ሲቀረፉ አጠቃላይ የህብረተሰብ ጤና ይሻሻላል።

የአፋር ህዝብ ፓርቲ (አህፓ) በቀጣይነት እስካሁን የተገኙትን አንጻራዊ ለውጦችን  ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስና ***"ጤና ለሁሉም"*** የሚለውን ግብ ዕውን ለማድረግ ጠንክሮ ይሰራል። የአፋር ህዝብ ፓርቲ በአፋር ክልል በጤናው ዘርፍ ያሉትን ክፍተቶች ለማካካስ ክፍተኛ ቱክረትና ርብርቦሽ እንደሚያስፈልግ ያምናል። በዋናነት የሚከተሉትን የጤና አገልግሎት መረሃግብሮች ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት ይሰራል።

- የእናቶችና የህጻናት የጤና አገልግሎትን በጥራት ማዳረስና ማጎልበት
- የክትባት መርሃግብሮችን በአግባቡ ተረዳሽ ማድረግና የክትትል ስርአቱን ማጠናከር
- የወባ በሽታን ለመከላከል የሚያስችል የሕብረተሰብ ጤና ትምህርትን ማስፋፋት
- የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋዎያን ማዕከላትን በየ ዞኑ ማቋቋም ፤
- በክልሉ ሆስፒታሎች የጤና አገልግሎት ጥራትና ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ፣
- አርብቶአደር ተኮር የጤና አገልግሎቶችን ማሳልጥና ማስፋፋት፤
- ተንከባካቢ፣ ሰው አክባሪ እና ርህሩህ የጤና ባለሙያዎችን ማፍራት ናቸው፡፡

እነዚህ አጀንዳዎች ተደጋጋፊነት ያላቸው ሲሆኑ የጤናውን ዘርፍ ዕድገትና ግብ ለማሳካት ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ናቸው፡፡ ባለፉት ሶስት አስርት ዓመታት የአፋር ክልል የጤና አገልግሎት አቅርቦትና ተደረሽነንትን በተመለከተ በኢትዮጵያ ከሚገኙ ክልልሎች የመጨርሻውን ሰንጠርዥ ይዞ ቀጥሏል። በኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲቱት አማካኝነት በተከታታይ በሚካሄደው የመሃበርሰብ ጤና ጥናት መሰረት የአፋር ክልል ከፍተኛ የህጻናት ሞት፣ ከፍተኛ እናቶች ሞት፣  እንዲሁም ዝቅተኛ የክትባት ተደራሽነትና በርካታ አሉታዊ የጤና አመላካች መለኪያዎች (health indicators) ከሚያስመዘግቡ ክልልሎች በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል። ይህ ተደጋጋሚ አሉታዊ የጤና ዉጤት የሚያመላክተው በአፋር ክልል የጤና ዘርፍ ልማት መርኃ ግብርና እስትራተጂ መሰረታዊ የጤና አገልግሎትን ለህብረተሰቡ ተደራሽ በማድረግ ረገድ የተደርገው ለውጥ እምብዛም መሆኑን ነው።

ለዚህም መሰናከል ሆነው ከሚጠቀሱ ጉዳዮች በዋናነት በጤናው ዘርፍ የሚካሄደው ብልሹና ሙስናን ተገን ያደረገ አሰራር፤ የሰለጠነ የጤና ባለሙያዎች እጥረትና ጥራት፤ የህዝቡን የአኗኗር ዘይቤ በቅጡ ያላገናዘቡ መመሪያዎችን እንደዋና ትግዳሮቶች ማስቀምጥ ይቻላል። በተለይ የአርብቶአደሩን ማህበረሰብ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ ከማድረግ አኳያ የተሰሩት ስራዎች ለብዙ ትችት የተጋለጡ ናቸው። ስለሆነም የአፋር ህዝብ ፓርቲ በአፋር ክልል በጤናው ሴክተር እና በአጠቃላይ በማሕበረሰቡ ልማትና አኗኗር ላይ እምርታዊ ለውጥ ለማድረግ የሚያስችል ፖሊሲና እስትራተጂ በሰፊው ነድፏል። ሆኖም አሁን ለሚካሄደው አገራዊ ምርጫ ሲባል ከተዘጋጀው ማኒፌስቶ ዉስጥ አንኳር አንኳር ነጥቦችን እናስተዋውቅ። ይህ እቅድ (ስትራተጂ) በየደረጃው ያለው አመራር፣ ባለሙያዎች፣እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሴክተር መስሪያቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ያላሰለሰ ጥረትና ትኩረት ሰጥተውት ተግባራዊ እንዲሆን የደረጋል፡፡

**የሕብረተሰብ ጤና (Public Health)**

የሕብረተሰብ ጤና (Public Health) ሁሉንም ዜጎች እኩል ተደራሽ የሚያደርግ የጤና መረብና ስልትን መገንባት ላይ ያተኩራል። ይህ ማለት ሁሉም ዜጋ ለጤንነት ተመሳሳይ ዕድሎች ሊኖሩት ይገባል ከሚል ሳይንሳዊ ጽንሰሃሳብ ይነሳል። የሕብረተሰብ ጤና ዋና አላማ ጤናማንትን ማስፋፋትና ማጎልበት እንዲሁም ለሽታ ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን ከሽታዎች መከላከል ነው ፡፡ የአፋር ህዝብ ፓርቲ የጤና ስትራተጂ ለጤና ወሳኝ ምሶሶዎች(Detrminants of Health) ማለትም የአንድን ግለሰብ መልካም ጤና ወይም ለበሽታ ተጋላጭነትን የሚወስኑ ምክንያቶችን መሰረት ያደርጋል። ከነዚህ ዉስጥ ለጤና ወሳኝ ናቸው ተብለው በሚታወቁና በሚከተሉት በሁለት ተያያዥ ሁኔታዎች ላይ ቅድሚያ በመስጠት እንሰራለን፤

- የአኗኗር ዜይቤና የባህሪ ለውጥ (behavioral change) ለማምጣት በሚከተሉት ባህሪዎች (ሲጃራ ማጨስ፤ ጫት መቃም፤ አልኮል መጠጣት) ላይ ያተኩራል።
- የጤና አገልግሎትን ማዳረስ (Health Service Delivery)

በክልላችን ብዙ ዜጎቻችን የተለያዩ ሱሶች ሰልባ በመሆናቸው በመሃበርሰብ ጤና ላይ የሚመጣው መዘዝና አደጋ በጣም ከፍተኛ ነው። በተለይ ጫት መቃምና ሲጃራ በማጨስ የወጣቱን ጤና ለመታደግና መጪዉን ትዉልድ ከሱሰኝነት ነጻ ማደረግ እንደ ዋና ዓላማ ያከናዉናል። የባህሪ ለውጥ ለማምጣት ከሃይማኖት ተቋማት፤ከሲቪክ ማህበራትና ከወጣቶች ሊግ ጋር አብሮ ይሰራል። የአፋር ህዝብ ፓርቲ በጤናዉ ዘርፍ መሰረታዊ የጤና አገልግሎቶችን ተደራሽነት፣ጥራትና ፍትሃዊነት ወደ ላቀ ደረጃ በማድረስ፤ የማህበረሰብ ባለቤትነትን በማሳደግና አገልግሎት ሰጪዎች ለሕዝቡ ያላቸውን ተጠያቂነት በመጨመር እንዲሁም ተቋማት ለተለያዩ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጡ በማስቻል ጠንካራና የማይበገር የጤና ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

- የአፋር ህዝብ ፓርቲ በቀበሌ ደረጃ ህብረተሰቡን በማደራጀት፤ የስነውሊድ አገልግሎት አቅርቦት፤ የክትባት አገልግሎትና የወባ በሽታን ለመከላከል የጽዳትና የአካባቢ ጥበቃን በጋራ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል። የማህበረሰብ ጤና ስርዓትን በማጠናከር ሕበረተሰቡ የግልና የጋራ ጤና ለማሻሻል አብሮ እንዲሰራ ያበረታታል። በተጨማሪም ዜጎች የግልና ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ሚያማስችል እቅዶችን ነድፎ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ይህም የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም እና የተደራጀ የጤና ልማት ሰራዊት በማጠናከር የሚፈጸም ይሆናል፡፡
- የአፋር ህዝብ ፓርቲ በየወረዳው ውስጥ ያሉ የመሰረታዊ ጤና አገልግሎት አሃዶችን (የጤና ጣቢያዎችንና ጤና ኬላዎችን) ወደ ከፍተኛ አፈጻጸም በማሸጋገር እና የመሰረታዊ ጤና አገልግሎቶችን ተደራሽነት እና ጥራትን በማሻሻል የህበረተሰቡን እርካታ ከፍ ያደርጋል፡፡ ይህም የአመራርና የአገልግሎት ሰጪዎችን ዕውቀት፤ ክህሎት አመለካከትና ሰነ-ምግባር፤ አደረጃጀትና አሰራሮችን እንዲሁም ፤የክትትልና ግምገማ ስርዓትን፣ የግበዓት አቅርቦትና ውጤታማ አጠቃቀም ሰርዓትን በመዘርጋት የጤና ተቋማት ትስስርን በማጠናከር የሚፈፀም ይሆናል፡፡

- ሁሉም ቤተሰብ በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድን ታቅፎ ዘላቂና ቀጣይ አባልና ተሳታፊ እንዲሆን በማድረግ ማንኛውም ሰው በገንዘብ እጦት ምክንያት የከፋ የጤና ችግር እንዳይደርስበት እንዲሁም በጤና ችግር ምክንያት ለኢኮኖሚ ቀውስ እንዳይዳረግ በማስቻል የጤና አገልግሎትን እኩል ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፡፡

- በክክልሉ የሚታየውን የመድሃኒት ጥራትና እጥረትን በመቅረፍ የመሰረታዊ መድሃኒቶች (Essential Drugs) አቅርቦት አስተማማኝነትን ያረጋግጣል።

- በአገራዊው የጤና ስርዓት ስታንዳርድ መሰረት አንድ ወረዳ በአማካይ 20 ጤና ኬላዎች፣ 4ጤና ጣቢያዎች እና አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል እንዲኖሩት የደርጋል፡፡

- አንድ ጤና ጣቢያ በስሩ ካሉት አምስት ጤና ኬላዎች ጋር እንደ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ እንዲተሳሰሩ በማድረግና የገጠር ጤና ጣቢያ በአማካይ ከ15,000-25,000 እንዲሁም በከተማ እስከ 40,000 ህዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን አንድ ጤና ኬላ ከ3,000-5,000 ህዝብ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

- ጤና ጣቢያ መሰረታዊ የጤና አገልግሎት ፓኬጆችን የሚሰጥ ሲሆን ከጤና ኬላዎች ለሚላኩ ታካሚዎች የሪፈራል ማእከልና የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የተግባር ማሠልጠኛ ተቋም በመሆን ያገለግላል፡፡

- አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል በአማካይ ከ60,000 እስከ 100,000 ህዝብ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

- የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል በጤና ጣቢያ ደረጃ ከሚሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ የመለስተኛና ድንገተኛ የቀዶ ህክምናና፤ ለህመምተኞች የደም መስጠት አገልግሎት (Blood Transfusion Service) ይሰጣል፡፡

- የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ከመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ ለሚላኩ ታካሚዎች የሪፈራል አገልግሎት መስጫና በእነዚህ ተቋማት ለሚሰሩ የጤና ባለሙያዎች የተግባር ማሰልጠኛ ተቋም በመሆን ያገለግላሉ፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን አሰራሮች ተግባራዊ በማድረግ ጥራት ያለዉ፤ ለሁለም የሚዳረስና ከተጠቃሚዉ የመክፈል አቅም ጋር የሚጣጣም የጤና አገልግሎት በክልሉ እንዲስፋፋ ይደርጋል።

- በአፋር ክልል ያሉ ሆስፒታሎች ደርጃቸውን በማሳደግና ጥራት ያለው የህክምና አገልግሎት እንዲሰጡ ይደርጋል።

- ጥራት ያላቸው መድሃኒቶች፤ የሊቦራቶሪ ምርመራ ማዕከሎች፤ ዘመናዊ የህምና ቁሳቁሶች አቅርቦትና አጠቃቀም እንዲጨምርና እንዲጎለብት ይደረጋል።

- በአፋር ክልል በመኪና አደጋና በግጭት ምክንያት ሰለባ የሚሆኑ ዜጎች ብዛት ከፍተኛ በመሆኑ በክልሉ ጥራት ያለው የአጥንት ጥገናና የአስቸኳይ ህክምና ማዕከል (Center of Excellence in Orthopedics & Emergency Medicine) እንዲገነባና አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል።

- በአርብቶ አደሩ ህብረተሰብ የጤና ፍላጎት ላይ ያተኮረ፤ በክልሉ የሚታየዉን የተዛባ የጤና አገልግሎት የሚያስተካክል የጤና ፖሊሲ ይተገበራል፤ ይህ ጥረት አስተማማኝ የእናቶችና የህጻናት የጤና አገልግሎት መርሃ ግብርን፤ የክትባት መርሃ ግብርን፤ የአልሚ ምግብ መርሃ ግብርን ያጠቃልላል፡፡

- ሥር የሰደደ የጤና አገልግሎት እጥረትን ለመቅረፍ የግል ባለኃብቶች በክልሉ የጤና ዘርፍ ላይ እንዲሰማሩ የማበረታታት ስራ ይከናወናለ።

- በአፋር ክልል የሚታየዉን የጤና ባለሙያዎች እጥረት ለማቃለል ተጨማሪ የጤና ባለሙያዎችን ማብቃት፤ እንዲሁም በስራ ሊይ ለሚገኙ ቀጣይ የስልጠና ዕድል እንዱያገኙ፤ የድጎማና የማበረታት መርሃግብሮችና ፖሊሲዎች ታግባራዊ ይደረጋል።

- ከውጭ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመተባበር የልምድ ልውውጥና የስኮላርሽፕ መርሃግብሮችን ያደራጃል ያሥፈጽማል።

- ሰመራ የጤና ኮላጅ የህክምና ዶክቶሮችን ለማሰልጠን እንዲችል ማብቃትና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ተግባራዊ ያደርጋል።

- የኤሌክትሮኒክ ቤተመጽሃፍት (ላይብራሪ) ይገነባል። የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶችን ማስፋፋትና በመገናኛ ብዙሃን (Mainstream media) በመጠቀም የስነወሊድና የህጻናት ጤና አያያዝን በተመለከተ በአፋርኛ የግንዛቤ ማስያዝ ትምህርት እንዲስፋፋ ይደረጋል።

- በክልሉ በጤና ዙሪያ የተሰማሩ ግብረሰናይ ድርጅቶች ወጥ የሆነ የአሰራር አካሄዴ በመቀየስ ከክልሉ ጤና ቢሮ ጋር በመተባበር ነባራዊ ክፍተቶችን እንዲሞሉ ይደረጋል።

- የልዩ ህክምና አገልግሎት (Especialist Medical Services) ማለትም የስኳር፤ የልብ፤ የጉበት፤ የደም ግፊትና የካንሰር ህክምና የሚሰጡ የግል ክሊኒኮች እንዲስፋፉ ለማበረታታት አስፈላጊ ትብብርና ድጎማ ለግል ባለሃብቶች ይደርጋል።

- የሕብረተሰብ ጤና ትምህርት በኤዴስ፤ በሳምባ ነቀርሳ፤ በወባ በሽታና የተመጣጠነ ምግብ እጥረትን ለመዋጋት የሚረዱ እርምጃዎች ይወስዳል።

**የአፋር ህዝብ ፓርቲን ይምረጡ ይለወጡ!!!**
**ምርጫ 2013**